**በወጣቱ ትውልድ ዘንድ የገንዘብ ቁጠባ ልምድ**
**እንዲዳብርና በትምሕርቱም ወደኮሌጅ ደረጃ እንዲደርስ፣**
**አቢሲኒያ ባንክ ያዘጋጀው ፕሮግራም**

ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ትምሕርት አግኝተው ራሳቸውን እንዲጠቅሙ፣ በየመስኩም አገራቸውን እንዲያገለግሉና አገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ በሚሄድ የዕድገትና የዘመናዊ ሥልጣኔ ጎዳና እንድትጓዝ፣ ቀደም ባሉት ዘመናት አያሌ መሪዎች በሚቻላቸው ሠርተዋል፡፡ ዛሬም ይህ ጥረት እንደቀጠለ ነው፡፡

ሆኖም የትምሕርት ዕድል ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በተስፋና በሕልም ደረጃ የሚገኝ እንጂ ተፈላጊውን ጥረት በማድረግ የሚደረስበት ሁኖ አይታይም፡፡ የከፍተኛ ደረጃ ትምሕርትን በተመለከተ ይህ ሁኔታ በይበልጥ አሳሳቢ ሁኖ ይታያል፡፡

የትምሕርት ዕድል እንዲህ አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት ብዙ ነው፡፡ የሕዝብ ቁጥር እየናረ መሄዱ አንደኛ ው እና ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ የመንግሥት የማስተማር አቅምም በሚፈለገው መጠን ሲያድግ አይታይም፡፡ በነዚህም ምክንያቶች ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር የሚያደርጉት የገንዘብ ወጭ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድ ግልጽ የሆኑ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ ወላጆች ይህንን በመገንዘብ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት ለመወጣት ከአሁኑ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ባንኮችና ሌሎችም ተቋሞች በዚህ ረገድ ወላጆችን የመርዳት ሃላፊነትም ዕድልም ይኖራቸዋል፡፡

ባሁኑ ጊዜ ባገራችን ውስጥ የሚገኘው የባንክ አሠራር ምንም እንኳ ከቅርብ ቀን ወዲህ በመስፋፋት ላይ የሚገኝ ቢመስል፣ በባንክ የመጠቀም ባሕል በኢትዮጵያ ውስጥ ገና አልተስፋፋም፡፡ እንዲስፋፋም መንግሥት ብቻ ሳይሆን ባንኮችም ጭምር ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሁሉ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አቢሲኒያ ባንክ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ፣ ረዘም ላለ ጊዜ በተግባር ላይ የሚውል አንድ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለተጠቃሚው ሕዝብ ለማቅረብ ተዘጋጅቷል፡፡

ከላይ እንደተጠቀመው የዚህ ፕሮግራም ዋነኛ ዓላማዎች ሁለት ናቸው፡፡

አንደኛው - የቁጠባ ባሕል በኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተስፋፋና እየዳበረ እንዲሄድ፣

ሁለተኛው - ወጣቶች ኮሌጅ ለመግባት ፈቃደኝነትና ችሎታ እያላቸው በገንዘብ ዕጥረት ብቻ እንዳይታቀቡ፣ ወላጆቻቸውና ዘመዶቻቸው እንዲሁም ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ቀደም ብለው የቁጠባ ሂሳብ ከፍተውላቸው በየጊዜው በጥቂት በጥቂቱ ገንዘብ እንዲያስገቡና ዋናውና ወለዱ ወጣቶቹ ኮሌጅ የመግባት ዕድል ሲያገኙ በዚህ ዓይነት ለረጅም ዓመታት የተጠራቀመው ገንዘብ በሙሉም ባይሆን በከፊል ወጭያቸውን እንዲችልላቸው ለማድረግ ነው፡፡

አቢሲኒያ ባንክ ይህንን ፕሮግራም ማዘጋጀት ከጀመረ ጥቂት ወራት አልፈዋል፡፡ በዚህ ፕሮግራም መሠረት ባንኩ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ አንድ ዓይነት ዕርዳታ ለማድረግ ወስኗል፡፡ ይህም ዕርዳታ በሚከተለው መልኩ ተቀርጾ ቀርቧል፡፡

1. አቢሲኒያ ባንክ፣ የባንኩ ደንበኞች ለሆኑ ወላጆች/ዘመዶች ቅድሚያ በመስጠት፣ እያንዳንዱ ወላጅ፣ ዘመድ ወይም ዕርዳታ ሰጭ ድርጅት በባንኩ ውስጥ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትና የፕሮግራሙ ተሳታፊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ወላጅ ዘመድ ወይም ዕርዳታ ሰጭ ድርጅት በዚህ ዓይነት ሂሳብ ውስጥ በወጣቱ ስም ገንዘብ ሲያስገባ፣ ባንኩ ደግሞ ያንኑ ያህል ገንዘብ ያስገባል፡፡ ዘመድ/ወዳጅ/ዕርዳታ ሰጭ ድርጅት አንድ ብር ሲያዋጣ ባንኩም አንድ ብር ያዋጣል ማለት ነው፡፡ ባንኩ የሚያዋጣው ገንዘብ ካቅሙ በላይ እንዳይሆን በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ድጋፍ ለአንድ ወጣት የብር 1,500 ጣሪያ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ወላጅ ለልጁ የኮሌጅ ትምሕርት የሚውል በየወሩ ብር **50** አስቀምጣለሁ ቢል፣ ባንኩም መዋጮው ብር 1,500 እስካላለፈ ድረስ ብር **50** ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ምሳሌ ሂሳቡ ሰ!ተመን የባንኩ መዋጮ (በወር ብር **50**) ለሰላሳ ወራት ይከፈላል ማለት ነው፡፡ የወጣቱ ወላጅ ከሰላሳ ወር በላይ በበኩሌ በየወሩ ብር **50** አስቀምጣለሁ ቢል ይህንን ለማድረግ ይችላል፡፡ የባንኩ መዋጮ ግን ብር 1,500 ሲደርስ ይቆማል፡፡

2. በዚህ ዓይነት የሚጠራቀመው ገንዘብ ዋናው ዓላማ የወጣቶች ትምሕርት ባጭሩ እንዳይቀጭና ማንኛውም ወጣት ትምሕርቱን ወደ ኮሌጅ ደረጃ የማድረስ ጠንካራ ተስፋ እንዲኖረው ለማድረግ ስለሆነ- የባንኩ መዋጮ ለኮሌጅ ወይንም ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል በኑላ ለተዘረጋ የመንግሥትን ዕውቅና ላገኘ የትምሕርት ፕሮግራም ብቻ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት ወጣቱ በሆነ ምክንያት ወደነዚህ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት ባይገባም- የራሱን ገንዘብ ከነወለዱ ይወስዳል፡፡ የባንኩ መዋጮ ግን አይሰጠውም፡፡

3. ከላይ እንደተጠቀሰው ወላጅ/ዘመድ በየወሩም ሆነ ባመቸው ጊዜ የሚያዋጣው ገንዘብ በአንድ በወጣቱ ስም በተከፈተ የቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ተቀምጦ በየወሩ ወለድ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ባንኩ በተመሳሳይ የሚያዋጣው ገንዘብም እንዲሁ በወጣቱ ልጅ ስም በተመዘገበ በየወሩ ወለድ በሚሰጥ በሌላ የቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ይቀመጣል፡፡ ፕሮግራሙ ጠቃሚነት የሚኖረው ለረጅም ዓመታት ሲቆይ ነውና÷ ወላጅ/ዘመድ ይህንን ፕሮግራም የሚጀምሩት ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት መካከል በሆኑ ልጆቻቸው/ ዘመዶቻቸው ቢሆን ይመረጣል፡፡

ለምሳሌ አንድ የ5 ዓመት ወጣት የዚህ ፕሮግራም ተሳታፊ ቢሆንና ትምሕርቱን ከአንደኛ ክፍል እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል አጠናቆ ወደ ኮሌጅ ቢገባ( ወላጆቹ/ዘመዶቹ ያስቀመጡለትና ባንኩ ያስቀመጠለት 3,000 ከነወለዱ ከአሥራ ሁለት ዓመት በኋላ ብር 6,121.76 ይሆናል፡፡ ድምሩ ከዚህ ሊያንስ የሚችልበት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ ብር 3,000 ባንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ ከተዋጣ፣ ወይም ደግሞ መዋጮው አጠር ላለ ጊዜ ብቻ ከተቀመጠ፣ ወይም መዋጮው ከብር 3,000 በታች ከሆነ፣ በመጨረሻ የሚገኘው ገንዘብ ከብር 6,121.76 ያንሳል፡፡

4. ወላጅ/ዘመድ ከራሱ ኪስ አውጥቶ በቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ያስቀመጠውን ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ ከነወለዱ የማውጣት መብት ይኖረዋል፡፡ ልጁ ኮሌጅ ሳይገባ ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል ቢወጣ፣ ባንኩም በዚያው መጠን መዋጮውን ያስቀራል፡፡ በችግር ወይም በሌላ ምክንያት በጥቂት ወላጆች ላይ ይህ ሁኔታ ሊደርስ እንደሚችል መገንዘብ ቢቻልም ሁኔታው በአብዛኛው ወላጅ/ዘመድ ላይ እንደማይከሰት ባንኩ ተስፋ ያደርጋል፡፡

5. ገንዘብ የሚጠራቀመው በወላጅ/ዘመድ ብቻ አይደለም፡፡ ወጣቱ ትንሽም ቢሆን በስጦታ ወይም ጊዜያዊ ሥራ በመሥራት የሚያገኛትን ገንዘብ በቁጠባው ሂሳብ ውስጥ አስቀምጦ ባንኩም እንዲያክልበት የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከላይ እንደተጠቀመው በጎ አድራጊ ድርጅቶችም ወጣቶችን ለመርዳት ቢፈልጉ እንዲሁ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6. ይህ የአቢሲኒያ ባንክ ፕሮግራም የተዘረጋው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩ ወጣቶች መሆኑ ግልጥ ነው፡፡ ውጭ አገር ያለ ቤተ ዘመድ/ወዳጅ ግን እዚህ ለሚማር ወጣት መዋጮ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ፕሮግራሙ በአዲስ አበባ ወይንም በጥቂት ጎልተው በሚታዩ ከተማዎች ተወስኖ እንዳይቀር አንድ ልዩ ጥናት በባንኩ ባለሙያዎች ተጠናቆ በመላው የኢትዮጵያ አስተዳደር እንዲዘረጋ ተወስኗል፡፡ ይህ የሚከናወነው በሚከተሉት ዝርዝር መስፈርቶች መሠረት ነው፡፡

<u>አንደኛ ፕሮግራሙ</u> ተግባራዊ የሚሆነው የባንኩ ቅርንጫፎች በሚገኙ ባቸው ከተማዎችና አካባቢያቸው ለሚገኝ ሕዝብ ነው፡፡

ሁለተኛ ፕሮግራሙ በከፊልም ቢሆን የሕዝብ ብዛትን መሠረት አድርጎ ዕድል የሚሰጣቸውን የወጣቶች ቁጥር ይወስናል፡፡

ሶስተኛ በመጀመሪያው ዙር የፕሮግራሙ ተሳታፊ ሊሆን የሚችል ማንኛ ውም ወላጅ/ዘመድ በባንኩ ውስጥ የቁጠባ ሂሳብ ከአንድ ዓመት በላይ ቀደም ባለ ጊዜ የተከፈተ መሆን አለበት፡፡ በሚቀጥሉት ዙሮች ለሚካሄደው ፕሮግራም ግን ወላጅ/ዘመድ ቀደም ሲል ቢያንስ ለአንድ ዓመት የቁጠባ ሂሳብ የከፈተ ደንበኛ መሆን አለበት፡፡

አራተኛ ፕሮግራሙ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ አምስት ዓመት ሆኖ፣ ከዚያ በኋላ ፕሮግራሙ ሊሻሻል/ሊለወጥ/ሊቋረጥ ይችላል፡፡

7. ፕሮግራሙ በገንዘብ ውሱን ስለሆነ፣ የፕሮግራሙ ተሳታፊ ለመሆን ዕድል የሚሰጣቸው ወላጆች፣ ዘመዶችና ወጣቶች በሎተሪ አሠራር ላይ በተመሠረተና በቅድሚያ በተዘጋጀ የዕጣ ቲኬት አሸናፊ የሆኑ ብቻ ናቸው፡፡ ያልተስተካከለ ወይም አድልዎ ያለበት ሁኔታ ቢከሰት ባንኩ አዲስ ዕጣ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ከባንኩ ሠራተኞችና ከደንበኞች የተውጣጣ የታዛቢ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

8. በአንድ ፊት የዕጣው አሸናፊ የሆኑ ወላጆች/ዘመዶች/ድርጅቶች የሚወክሉት ሰው በሌላ በኩል ደግሞ ባንኩ የወከለው አንድ የባንኩ ሠራተኛ ሁለቱንም ወገኖች ግዴታ የሚያስገባ ዝርዝር የሆነ ውል በምስክር ፊት እንዲዋዋሉ ያደርጋሉ፡፡

9. አሁን በምንገኝበት የባንኩ የበጀት ዓመት ውስጥ (ማለትም እ.አ.አ በ2000/2001) በዚህ ፕሮግራም የሚሳተፉ ከተማዎችና አካባቢዎች እንዲሁም ዕድል የሚያገኙ የፕሮግራሙ ተሳታፊ ደንበኞች ቁጥር እንደሚከተለው ተወስኗል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባና አካባቢዋ | 160 ወጣቶች | ብር 240,000.00 |
| ባህር ዳርና አካባቢዋ | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 |
| አዋሳና አካባቢዋ | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መቀሌና አካባቢዋ | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 | |
| ጎንደርና " | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 | |
| ጅማና " | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 | ቅርንጫፍ ሲከፈት |
| ድሬደዋና " | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 | ቅርንጫፍ ሲከፈት |
| ናዝሬትና " | 60 ወጣቶች | ብር 90,000.00 | ቅርንጫፍ ሲከፈት |

በፕሮግራሙ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች ቢነሱ፣ በስልክ ቁጥር 51 41 30 ማነጋገር ይቻላል፡፡